## 1. <u>በፕሮግራሙ የታቀፉ ደርጅቶች መበት (የሚያገኙት ጥቅም)</u>

በአሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት አልፈው በፕሮግራሙ የሚታቀፉ ድርጅቶች የሚከተሉትን ጥቅሞች ያገኛሉ።

- ❖ በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የመስተናገድ፣
- ❖ የድህረ ክፍያ (የቀረጥና ታክስ ክፍያ የዱቤ መስተንግዶ) አገልግሎት፣
- ❖ ለ30 ቀን የሚቆይ በኮፒ ሰነድ የመስተናገድ፣
- ❖ የቅድመ እቃ አወጣጥ አገልግሎት፣
- ❖ ማንኛውንም የጉምሩክ አገልግሎት በራሳቸው መጋዘን የማግኘት፣
- ❖ ቀለል ያለ ዲክረላራሲዮን የመጠቀምና ቀላል የጉምሩክ አገልግሎት፣
- ❖ ለፍተሻ ከተመረጡ በመረጡበት ቦታ የቅድሚያ ፍተሻ አገልግሎት፣
- ❖ ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም አርማ የመጠቀም፣
- ❖ በማንኛውም የጉምሩክ አገልግሎት የቅድሚያ አገልግሎት የማግኘት፣
- ❖ የሚወጡ ህጎችን እና አሰራሮችን ከመፅደቃቸው በፊት አስተያየት የመስጠት፣
- ❖ በሁሉም የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቅድሚያ አገልግሎት ያገኛሉ።

## 2. <u>በፕሮግራሙ የታቀፉ ድርጅቶች ግዴታ</u>

የመብቱ ተጠቃሚ ድርጅቶች የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው።

- ➢ የተሰጠውን መብት አለ አግባብ ያለመጠቀም፣
- ➢ የገቢም ሆነ ወጪ እቃዎች ለፍተሻ ሲመረጡ ተባባሪ የመሆን፣
- ➢ የስነ ምግባር ችግር ያለባቸው ሰራተኞች ላይ እርምጃ የመውሰድ፣
- ➢ በጉምሩክና ሀገር ውስጥ ገቢ የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ በወቅቱ የመክፈል፣
- ➢ የውስጥ አሰራርና የስራ ቦታ ለውጥ ሲያደርግ በወቅቱ የማሳወቅ፣
- ➢ ችግሮችን በየወቅቱ ሪፖርት የማድረግ እና በጋራ ለመፍታት ዝግጁ መሆን፣
- ➢ በኦዲተሮች የሚሰጡ የማስተካከያ ምክረ ሃሳቦችን መተግበርና ተገቢውን የአሰራር ማሻሻያ ማድረግ፣
- ➢ ድርጅቱ ለድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ሲመረጥ አስፈላጊ ሰነዶችን በማቅረብ ለኦዲት ስራው ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣


*By Talema Ayele, Email address iffso143@gmail.com, Mob. Number 09-12-75-96-55, AEO principal officer*